# በፓሪሱ የተቃዋሚዎች ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ተጠቃለለ

## ተቃዋሚዎችን የሚያስተባብር የተቃዋሚዎች ሕብረት ተመሠረተ

አርብ ከመስከረም 1 ቀን 1991 ዓ.ም እስከ እሁድ መስከረም 3 ቀን 1991 ዓ.ም ለሶስት ቀናት በከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት እየተንፀባረቀበት የተካሄደው የፓሪሱ የተቃዋሚ ኃይሎች ጉባኤ የተለያዩ የውሳኔ ሀሳቦችን በማፅደቅና የተቃዋሚ ኃይሎችን ኅብረት ለመመስረት የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍ እሁድ እኩለ ሌሊት በታላቅ ድምቀት መጠናቀቁን ከስፍራው የቤዛ ጋዜጣ ልዩ ዘጋቢ የላከልን ዘገባ አስረዳ፡፡

በፈረንሣይ ሀገር በፓሪስ ከተማ ለሶስት ቀናት የተካሄደውን ጉባኤ በማዘጋጀት በስኬት እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ የሆነ ጥረት ያደረገው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) አባል ድርጅት የሆነው በዶክተር ነገደ ጎበዜ የሚመራው የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) አመራሮች ያላሰለሰ ጥረት ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይሎች ሕብረት እንዲመሠረት የሚያስችል መሠረት የሚለው የፓሪሱ ጉባኤ ላይ ይገኛል ተብሎ ሲጠበቅ ሳይገኝ የቀሩት መአህድና አነግ በስተቀር በ1985 ዓ.ም በፓሪስ በሁለት አለምአቀፍ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ፀረ ረሀብ የልማት ኮሚቴና የሰውልጅ እድገት ተራድኦ ተደርጎ በነበረ ጉባኤ ማብቂያ ላይ የተመሰረተው ድርጅቶች ተወካዮች እንዲሁም ከ30 በላይ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮችና ታዛቢዎች መገኘታቸውን ከፓሪስ የደረሰን የዘጋቢያችን ዘገባ ያስረዳል ፡፡

የቤዛ ልዩ ዘጋቢ የፓሪሱ ጉባኤን መካሄድ እንድዲሁም አላማውንና ግቡት በተመለከተ የጉባኤው አዘጋጆችን አነጋግሮ ነበር፡፡ ከጉባኤው አዘጋጆች ይህ ሶስት ቀናት የፈጀው ጉባኤ ማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያት የኢትዮጵያ ችግሮች በሙሉ በዲሞክራሲያዊ ዘዴ ተፈተው ሀገሪቱና ህዝቧ የሰላምና የዲሞክራሲና የአንድነት ፊር ይዘው እንዳይጓዙ እስካሁን እንቅፋት ሆነው ከቆዩት ምክያቶች አንድ ተቃዋሚ ኃይሎች ተአማኒነት ያላቸው አማራጮች በጋራ ለማቅረብ ለዚህም በጋራ ለመታገል ባለመቻላቸው እንደሆነ ግልፅ በመሆኑ በውጭ የሚገኙና በሀገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎች የሚሳተፉበትና የመወያያ አጀንዳችውን በሀገሪቱ የተጨናገፈውን የዲሞክራሲያዊ ሂደት እንዲስተካከል የተቃዋሚ ድርጅቶች የጋራ ሕብረት የሚጠናከርበትንና የሀገሪቱ ሉዓላዊነት መደፈረን በተመለከተ አንድ አቋም ላይ ለመድረስ የሚያስችል የጋራ የትግል ስልት ለመቀየስ ያስችል ዘንድ የታህሳስ 1986 ዓ.ም የግዩኑ የሰላምና እርቅ ጉባኤ ይካሄድ ዘንድ አስተባባሪ ኮሚቴ እዚህ ፓሪስ ውስጥ በማቋቋም ተንቀሳቅሶ ከነበረው የአስተባባሪ ኮሚቴው አባል ድርጅቶች መካከል የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ), የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር (ታንድ),
የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድህን), የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢድኃቅ),
የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ህብረት,
የትግራይ ትግሪኝ ኢትዮጵያ በአሁኑ አጠራሩ የኢትዮጵያውያን ቡድን ለሶሻል ዴሞክራሲ አመራር አባላት በሆላንድ ዋና ከተማ አምስተርዳም ከሰኔ 20 እስከ ሰኔ 21 ቀን 1990 ዓ.ም ባደረግነው ጉባኤ ማብቂያ ላይ ባሳለፍነው ባለ ሰባት ነጥብ ውሳኔ ሀሳቦች መሠረት ነው ጉባኤውን ከመስከረም 1 ቀን እስከ መስከረም 3 ቀን 1991 እንዲካሄድ የጠራነው፡፡
የአመስተርዳሙ ጉባኤያችን ያሳለፋቸው ሰባት የውሳኔ ነጥቦች

1. መሠረታዊ በሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ውዥንብርና የተሳሳተ የትግል አቅጣጫዎች ከያለበት መስንዘራቸው ለትግሉ ጥራትና ርምጃ እስጊ መሆናቸውን በመገንዘብ ሰባቱ የፓሪስ ጉባኤ አስተባባሪ አባል ድርጅቶች በወቅቱ የተስማሙባቸውን አቋሞች እንደገና የማደሱን ጉዳይ አንገብጋቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም አስተባባሪ ኮሚቴ ለታህሳሱ የአዲስ አበባ የሰላምና እርቅ ሀገር አቀፍ ጉባኤ ባሰናዳው ሰነድ ላይ በዲሞክራሲና በነፃ ምርጫ በሕገመንግሥት ሂደትና መሠረታዊ ይዘት,
   በብሔረሰቦች መብትና በኢትዮጵያ አንድነት ሉዓላዊነት ጥያቄ አስፍሯቸው የነበሩትን የፖለቲካ አቋሞች እንደገና መርምሮ በማፅደቅ ለነዚህ ዓላማዎች በጋራ ለመታገል,
2. በነዚህ መሠረታዊ አቋሞች በመመራት አሁንም በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ኢትዮጵያውያን በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ የብሔሮችና የብሔረሰቦችን መብት የተረጋገጠበት የሰው ልጅ መብቶች ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠበት የሰው ልጅ መብቶች ሙሉ በሙሉ የተረከበሩበት የህግ የበላይነት እውን የሆነበትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትተዳደር ሀገር ለመመስረት ለነፃ ምርጫና ለዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት በጋራ ለመታገል,
3. ዛሬ በኢትዮጵያበተተከለው ፀረ ሕዝብና ፀረ ዲሞክራሲያዎ አገዛዝ ስር ነፃ ምርጫው ሆነ ዴሞክራሲያአ ሕገመንግሥትን መጠበቅ የማይታሰብ ጉዳይ በመሆኑና እነዚህ እውን እንዲሆኑ በቅድሚያ ለዲሞክራሲ አመቺ የሆነ ኃይል ሚዛን በትግል ከመፍጠር ሌላ አማራጭ እንደሌለ በመገንዘብ ለዴሞክራሲ ሂደት መጎልበትና ለነጻ ምርጫ መካሄድ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር በጋራ ለመታገል,
4. ለዴሞክራስ ሂደትና ነጻ ምርጫ ዓለምአቀፋዊ መስፈርቶችንና መርሆዎች ያቀፉ ሰነዶችን እንደገና በመመርመር የሚሻሻለውን አሻሽለን,
   የሚዳብረውን አዳብረን አንድ የጋራ የመታገያና የማታገያ ሰነድ ይዘን በጋራ ለመራመድ,
5. በፓሪሱ አስተባባሪ ኮሞቴ መሠረታዊ የፖለቲካ አቋሞችና ነጻ ምርጫንና ዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥትን አስመልክተን በምንነድፈው የጋራ ሰነድ በመመርኮዝ በሌሎች ዲሞክራሲያዊ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር

ውይይት በመክፈት የነሱም ገምቢ አስተዋፅኦ በታከለበት አማራጭ ሰነድ አማካይነት የኢትዮጵያ ዴሞክራቶ
ች በሙሉ በጋራ እንዲታገሉ ጥሪ ለማድረግ,

6. ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጪ ያሉ የሲቪክ ማኅበራትና ዲሞክራሲያዎ ዜጎች ሁሉ ለዚህ የጋራ ትግል ገንቢ አስተ
ዋፅኦ እንዲያደርጉና ህዝቡን ከዳር እስከ ዳር በማንቀሳቀስ የዜግነት ግዴታቸውን የሚወጡባቸውን የድጋፍ መ
ዋቅሮች የሚዘረጉባቸውን ዘዴዎች ለመሻት,
7. እነዚህ ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን ጥንስሶች መልክና ይዘት ዘርዘር ባለ ሁኔታ አቀነባብረን ለማቅረብ ለጊዜ ከፓ
ሪስ ጉባኤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተያያዙትን የቀድሞ አስተባባሪ ኮሚቴው አባል የነበረውን የኦሮሞ ነፃነ
ት ግንባር (ኦነግ) በተጨማሪ የመላ አማራ ህዝብ ድርጅቶችን (መአህድ) እና የኢትዮጵያ የሰላምና የዲሞክራሲ
አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትን የሚያካትት አንድ ጉባኤ ባጭር ጊዜ ውስጥ ለመጥራት ተስማምተናል።

ሲሆኑ እነዚህን ነጥቦች እንደጉባኤው አጀንዳነት በመያዝ 22 የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች በአዲሱ የሳተላይት,
የቴሌፎን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሰኔ 14 ቀን 1990 ዓ.ም ባደረጉት ውይይት እንዲሁም ሐምሌ 24 ቀን 1990 ዓ.ም በጀ
ርመን ፍራንክፈርት በተካሄደ የኢትዮጵያውያን ጉባኤ ማብቂያ ላይ በተደረሱት የውሳኔ ሀሳቦች መሠረት ጠንካራ የተቃ
ዋሚዎች ኅብረት ለመመስረት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለዚህ የፓሪሱ ጉባኤ ስኬታማነት ከፍተኛ
አስተዋጽኦ አድርገዋል ስሉ ለጋዜጣው ዘጋቢ ገልፀዋል።

እሁድ መስከረም 3 ቀን 1991 ዓ.ም እኩለ ለሊት ላይ የቀድሞው የፈረንሣይ ሶሻሊስት ፓርቲ ዋና ፀሐፊ በአሁኑ ወቅት
የአውሮፓ ፓርላማ የልማትና ትብብር ኮሚሽን ፕሬዝዳንትና የቀድሞው የፈረንሣይ ጠቅላይ ሚኒስትር በሚስተር ማይ
ክል ሮካር የመዝጊያ ንግግር ተጠናቋል።

ከመስከረም 1 ቀን እስከ መስከረም 3 ቀን 1991 ዓ.ም በፓሪስ በተካሄደው ጉባኤ ላይ አዘጋጅነቱን በኃላፊነት የሚመሩ
ት ዶክተር ነገደ ጎበዜ ስለጉባኤው አስመልክተው ከልዩ ዘጋቢያችን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለፁት የኢህአዴግ
መንግሥት ለዲሞክራሲያዊ ስርአት በሀገሪቱ መስርቻለሁ ይላል,
ነፃ ምርጫ አካሂጃለሁ ይላል። በተቃዋሚዎች በኩል ደግሞ በአለምአቀፍ መስፈርቶች አማካኝነት የዲሞክራሲ ስርዓት
መተካት መሟላት አለባቸው በሚል ተሰባስበን ተወያይተን ነበር። አሁን በዚህ ጉባኤ ሁላችንም መክረን አንድ ሰነድ ጨ
ብጠን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ ለማቅረብም ነው።

የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት እንዲሁም ኦነግ እዚህ ጉባኤ ላይ የማይገኙበትን ምክንያት የገለፁ ቢሆንም የመአህድ ጉ
ዳይ ግን ግራ የሚያጋባ ነው በማለት አብራርተዋል።

በዚህ የጋራ ሰነድ ጨብጦ ያበቃው ጉባኤ የተቃዋሚ ኃይሎች የጋራ ትግል ስልትም ይቀየሳል ተብሎ የሚታመን ሲሆን
መአህድ ከጦርነት እወጃ ውጪ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር ብቻ ትብብር ይፈጥራል ሲሉ በፓሪሱ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ምክን
ያቱን ቢገልፅም የጉባኤው አጀንዳ ከትጥቅ ትግል ውጪ የሆነ አጀንዳ እንደሆነ ተናግረዋል።

<u>ከቤዛ መስከረም 5 ቀን 1991</u>